JUSTICE WITH CHILDREN
www.justicewithchildren.org

# ዓለም አቀፍ መግለጫ በስራ ላይ የሕጻናት ፍትህ

እ.ኤ.አ ህዳር 20 ቀን 2021

እ.ኤ.አ የ2021 የዓለም አቀፍ የሕጻናት ፍትህ ጉባኤ፤

“ የፍትህ ተደራሽነትን ለሁሉም ሕጻናት ማረጋገጥ-መድልኦ ወደሌለበትና አካታች ወደሆነ የሕጻናት የፍትህ ሥርዓት” በሚል መሪ ቃል ከ100 ሀገራት የተውጣጡ ሁሉንም ትውልድ የሚወክሉ ቁጥራቸው ከ4,800 በላይ የሆኑ ተሳታፊዎች እ.ኤ.አ ከህዳር15-20፤ 2021 በበይነ-መረብ አማካኝነት በመሰባሰብ ፤

ቴር ዴስ ሆምስ ***(Terre des homes)*** ፣ ፔናል ሪፎርም ኢንተርናሽናል (Penal Reform International)፣ ኢንተርናሽናል አሶሲዬሽን ኦፍ ዩዝ ኤንድ ፋሚሊ ጀጅስ ኤንድ ማጂስተሬትስ (the International Association of Youth and Family Judges and Magistrates) እና ኢንተርናሽናል ኢስቲቱይት ፎር ዘ ራይትስ ኦፍ ዘ ቻይልድ (the International Institute for the Rights of the Child) የተባሉ ተቋማትን በጥምረት በያዘው በዓለም አቀፉ የሕጻናት ፍትህ ጥምረት (the Global Initiative on Justice With Children) አዘጋጅነት፤ በሜክሲኮ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት (the federal Mexican Supreme Court of Justice) አስተናጋጅነት፤ በተባበሩት መንግስታት የሕጻናት ፈንድ (the United Nations Children’s Fund) ፤ በተባበሩት መንግስታት በህፃናት ላይ የሚደርስ ጥቃት ዋና ፀሃፊ ልዩ ተወካይ (the Office of the Special Representative of the United Nations Secretary-General on Violence Against Children) ፣ በተባበሩት መንግስታት የአደንዛዥ ዕፅ እና የወንጀል ቢሮ (the United Nations Office on Drugs and Crime)፣ በተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር ቢሮ (the Office of the United Nations High Commissioner for Human Rights) ፤ በኢኮኖሚ ትብብር እና ልማት ድርጅት (the Organisation for Economic Co-operation and Development) እና በፓዝ ፋይነደርስ ፎር ፒስፉል፤ ጀስት ኤንድ ኢንክሉሲቭ ሶሳይቲስ (the Pathfinders for Peaceful, Just and Inclusive Societies) የቴክኒክ ድጋፍ፤ በአውሮፓ ምክር ቤት እና በአውሮፓ ፓርላማ (the Council of Europe and the European Parliament) ድጋፍ ፤ በቤከር ማክኬንዚ Baker (McKenzie) የበጎ ፍቃድ ድጋፍ እንዲሁም በሳይንቲፊክ ኮሚቴ (the Scientific Committee)፣ በኮሚቴ ኦፍ ኦነር (the Committee of Honour)፣ በሕጻናት እና ወጣቶች አማካሪ ቡድን (the Child and Youth Advisory Group) እንዲሁም ከዓለም አቀፉ ጉባኤ በፊት አህጉር እና በሀገር ደረጃ በተደረጉ የመሰናዶ ገባኤዎች የተሰጡ ግብዓችን መሠረት በማድረግ፤

በተባበሩት መንግስታት የሕጻናት መብቶች ኮንቬንሽን እና በሌሎች ተዛማጅ ዓለም አቀፍ የሕጻናት መብቶች መስፈርቶች ውስጥ የተካተቱትን የሕጻናት መብቶች ለማስተዋወቅ፣ ለመጠበቅ እና ለማሟላት ተወስደው የነበሩ ተጨባጭ ቁርጠኝነቶችን በድጋሚ በማረጋገጥ፤

ፍትህ ለሕጻናት፤ *restorative justice* እና የሕጻናት ፍትህ ሥርዓትን ማጠናከር የሚሉ ርእሰ ጉዳዮች ዙሪየ ቀደም ሲል በተካሄዱ ሶስት ዓለምአቀፍ ጉባኤዎች በተቀመጡት የፓሪስ መግለጫ (ፈረንሳይ፣ እ.ኤ.አ ግንቦት 2018)፣ የጄኔቫ መግለጫ

(ስዊዘርላንድ፣ እ.ኤ፣አ ጥር 2015) እና የሊማ መግለጫ (ፔሩ፣ እ.ኤ.አ ህዳር 2009) መሠረት የተገቡትን ቃል ኪዳኖች በማስታወስ፤

ከዘላቂ ልማት ግብ 16 ጋር በተገናኘ በፓዝ ፋይንደርስ ፎር ፒስ፤ ጀስትና ኢንክሊሲብ ሶሳይቲስ *(the Pathfinders for Peaceful, Just and Inclusive Societies)* አማካኝነት በአለም አቀፍ፤ በአህጉር አቀፍና በሀገር አቀፍ ደረጃ ባሉ የተለያዩ መንግስታት እና ሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት እንዲሁም በትምህርት ተቋማት የተዘጋጀውንና ተቀባይነት ያገኘውን በዓለም አቀፉ የፍትህ ለሕጻናት የድርጊት ጥሪ (the global Justice for Children Call to Action) (እ.ኤ.አ መስከረም 2019) ውስጥ የተመለከቱተን ምክረ ሀሳቦች እና የተግባር ነጥቦችን በመደገፍ፤

በቀድሞው የዓለም አቀፍ ጉባኤ (ፈረንሳይ፤ እ.ኤ.አ ግንቦት 2018) በሕጻናትና በወጣቶች ለቀረቡት ጥያቄዎች በድጋሚ አፅንኦት የመስጠት አስፈላጊነትን፤ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ነጻነታቸውን ስለተነፈጉ ሕጻናት በተደረገው ዓለም አቀፍ ጥናት (እ.ኤ.አ ህዳር 2019) ውስጥ የተቀመጠውን መመሪያ አስፈላጊነት፤ ኮቪድ-19 በሕጻናት ፍትህ የማግኘት መብት ላይ የሚያስከትለውን ጫና በተመለከተ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የተዘጋጀውን አጭር የፖሊሲ መግለጫ፤ ኮቪድ-*19* በሕጻናት ላይ እያስከተለ ስላለው ተጽዕኖ *(እ.ኤ.አ ሚያዚያ 2020)* እና የተለያዩ ተቋማት በህብረት ሆነው ኮቪድ-*19* እና ነጻነታቸው የተነፈጉ ሕጻናት *(እ.ኤ.አ ሚያዚያ 2020)* በሚል ርዕስ ያወጡትን ሞያዊ ማስታወሻ፤ ፤ በኮቪድ-*19* ዘመን የሕፃናት ፍትህ ተደራሽነት በሚል ርዕስ በተባበሩት መንግስታት የሕጻናት ፈንድ ከቀረበው የተወሰዱ ትምህርቶችን፤ ከመስከ የተወሰዱ ትምህርቶችን *(እ.ኤ.አ ታህሳስ 2020)* እና ወንጀልን መከላከልና የወንጀል ፍትህ አስተዳደር በሚል በተዘጋጀው አስራ አራተኛው የተባበሩት መንግስታት ጉባኤ ላይ በሀገራትና በመንግስታት መሪዎች፤ በሚኒስትሮች እንዲሁም በተባበሩት መንግስታት ድርጅት አባል ሀገራት ተወካዮች ወንጀልን በመከላከል፤ በወንጀል ፍትህ አስተዳደርና በህግ የበላይነት ላይ በኮዮቶ ባወጡት መግለጫ *(ጃፓን፤ እ.ኤ.አ መጋቢት 2021)* የገቡትን ቃል ኪዳን በመገንዘብ፤

የሚከተሉትን አስቀምጠዋል፤

1. የፍትህ ተደራሽነትን ወይም መፍትሄዎቹን በተመለከተ የተባበሩት መንግስታት የሕጻናት መብቶች ኮንቬንሽን ምንም እንኳን ቀጥተኛ የሆኑ ቃላትን በመጠቀም ያልገለፃቸው ቢሆንም፤ ፅንሰ ሀሳቡ ግን የሕጻናት ጥቅምን በማስቀደም መርህ ውስጥ፤ በሕጻናት መረጃን በማግኘት፡ ሀሳብን በመግለፅ እና በመሰማት መብት ውስጥ፤ ከሁሉም ዓይነት ጥቃት በመጠበቅ መብት ውስጥ፤ በወንጀል ውስጥ ገብተው ለተገኙ እና ከህግ ጋር ንክኪ ላላቸው ሕጻናት በተደነገጉት መብቶችና ጥበቃዎች ውስጥ እና ነፃነትን ከመንፈግ ጋር በተያያዘ በተቀመጡ የመፍትሄ እርምጃዎች እና በሌሎች ድንጋጌዎች ውስጥ እንዲሁም የጥቃት ተጎጂዎችን ስለማገገምና መልሶ ስለማቋቋም በተደነገጉት ድንጋጌዎች ውስጥ ታሪካዊ በሆነ መልኩ ተካትቶ ይገኛል።

2. የዓለም አቀፉ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ እና የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ የቃልኪዳን ሰነድ( ሌሎችንም ጨምሮ) በሁሉም ሕጻናት ላይ በእኩልነት ተፈጻሚ እንደሚሆኑ እና ማንኛውም መብቱ ወይም ነጻነቱ የተጣሰበት ሰው ተገቢ መፍትሄ የማግኘት መብት እንዳለው እና ይህ መብቱም ብቃት ባለው የዳኝነት፣ የአስተዳደር ወይም የሕግ አውጭ አካል ወይም በሌላ ብቃት ባለውና የህግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ሊወሰንለት እንደሚገባ ተደንግጓል።

3. አድሎአዊ አሰራርን የሚኮንነው መርህ የሕጻናት መብቶች ኮንቬንሽን መሰረታዊ ምሰሶ ከመሆኑም በላይ ለበርካታ ዓለም አቀፍ፣ አህጉራዊ እና ሀገራዊ የህግ ሰነዶች መሠረት ሆኖ እያገለገለ ይገኛል።

4. የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አባል ሀገራት በተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ፍትህን በእኩልነት የማግኘት መብት የሁሉም (ሕጻናትን ጨምሮ) መሠረታዊ መብት መሆኑን ተቀብለዋል፤ እንዲሁም ፍትህን ለሁሉም በእኩልነት ማድረስና በሕጻናት ላይ የሚፈፀምን የሀይል ጥቃት ማስቆም እ.ኤ.ኤ የ2030 ዘላቂ የልማት አጀንዳ (በተለይም የግብ 16) ማእከላዊ ጉዳዮች መሆናቸውን አረጋግጠዋል።

5. በፍትህ አውድ ውስጥም ሆነ ከፍትህ አውድ ውጭ ያሉ ሕጻናት እየደረሱባቸው ላሉ ቁጥር ስፍር ለሌላቸው የጥቃት ዓይነቶች እና በህብረተሰቡ ውስጥ ላሉ ውድቀቶች ኃላፊነቱን እንዲወስዱ እየተገደዱ ሲሆን፤ ይህም የተገለሉ ሕጻናትን በከፍተኛ ሁኔታ የሚጎዳ ከመሆኑም በላይ ሕጻናት ተጎጂ፤ ከሳሽ ወይም ተከሳሽ ፤ ምስክር ወይም እንደእነዚህ እንደሁሉም ወይም በሌላ በማናቸውም አቋም ከህግ ጋር እንዳይነካኩ ለመከላከል ወይም ሲነካኩ ሊገጥማቸው የሚችል ስጋትን ለመከላከል ወይም ምላሽ ለመስጠት የሚደረገውን ጥረት ወደኋላ ይጎትታል፤

6. የኮቪድ-19 ወረርሽኝ  የነበረውን ማህበራዊ አለመመጣጠን ይበልጥ አጉልቶታል፤ ቀድሞም ደካማ የነበረውን የሕጻናት ፍትህ እና ጥበቃ ሥርዓት እና አገልግሎት አዳክሟል ወይም ሙሉ ለሙሉ ሽባ አድርጓል፤ እነዚህ ችግሮችም በአየር ንብረት ለውጥ እና በአካባቢያዊ ቀውሶች፣ በድንበር ውጥረቶችና በጦርነቶች፣ በኢኮኖሚ ቀውስና በሌሎች የሰብዓዊ አደጋዎች እንዲሁም በሌሎች ቁጥራቸው እጅግ በጣም ብዙ በሆኑ ወቅታዊና ቀጣይነት ባላቸው ቀውሶች ተባብሰዋል፤ ይህም ለሁሉም ሕጻናት ፍትህን በዘላቂነት ለማድረስ የሚያችሉ፤ ችግርን ተቋቁመው መዝለቅ የሚችሉማእቀፎችን፣ ሥርዓቶችን እና አሰራሮችን መገንባት ይጠይቃል።

7. ዓለም ስለማህበራዊ፣ ስለሥርዓተ-ፆታ፣ ስለዘር፣ ስለአየር ንብረት እና ስለፖለቲካ ፍትህ ግንባር ቀደም በመሆን በሀገር አቀፍም ሆነ በዓለም ደረጃ እየጠየቁ ያሉ እና በዚህም የክርክር አቅጣጫዎችን እያስቀየሩ እና የፍትህ ሥርዓት ለውጥ እንዲመጣ ጫና እያሳደሩ ያሉ አያሌ አቅም ያላቸውን ሕጻናትና ወጣቶችን በብዛት እያየች ትገኛለች።

8. በሕጻናት የፍትህ ስርዓት ውስጥ እና ፍትህን በማድረስ አገልግሎት ውስጥ አድሎአዊ አሰራር እና በእኩልነት አለመታየት አለመኖር ሁሉም ሕጻናት ማንነታቸው፤ የመጡበት አካባቢ ወይም ያሉበት ሁኔታ የልዩነት ምክንያት ሳይሆን በእኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል።

9. ከህግ ጋር ንክኪ ያላቸው ሕጻናት በተፈጥሯቸው ማንኛውም ሕጻን ያለው መብት ሁሉ አላቸው፤ ይህም በተለየ ሁኔታ ተጋላጭ ለሆኑ ሕጻናት ትኩረት በመስጠት እና የእያንዳንዱን ሕጻን ልዩ ፍላጎት እንዲሁም የእድገት ደረጃ ከግምት በማስገባት መብቶቻቸውን እና ደህንነታቸውን በእኩልነት እና በፍትሃዊነት ማክበርና መጠበቅን አስፈላጊ ያደርገዋል።

10. ፍትህን፣ የህፃናት ጥበቃ እና ደህንነትን፣ ማህበራዊ ጥበቃን፣ ትምህርትን እና ጤና አጠባበቅን እንዲሁም ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን የሚያስተዳድሩ ሥርዓቶች ከህግ ጋር በማንኛውም መልኩ ንክኪ ላላቸው የሕጻናት ጉዳዮች በተሟላ እና ውጤታማ በሆነ  መልኩ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችላቸውን የቅንጅት እና የትብብር አሰራሮችን ማጠናከር ግድ ይላቸዋል።

በአለም ጉባኤ የሕጻናት እና ወጣቶች አማካሪ ቡድን አማካኝነት ተሰብስበው የነበሩ የሚከተሉትን የሕፃናት እና የወጣቶች ድምጽ ያከብራል።

11. እኛ ከፍትህ ሥርዓቱ ጋር ንክኪ ስላላቸው ሕጻናት መብቶች ልዩ ስሜት ያለን የሕጻናትና ወጣቶች ስብስብ ነን፤ ለዚህም ምክንያቱ አብዛኞቻችን በእነዚህን ሥርዓቶች ውስጥ ራሳችን ያለፍንባቸው በመሆኑ ነው፤ ከዚህ ልምዳችን በመነሳትም፤

    ሀ. ከትውልድ ትውልድ የሚሻገር አድሎአዊ አሰራር እና የኢኮኖሚ አለመመጣጠን ሕጻናት ከህግ ጋር ንክኪ እንዲኖራቸው የሚያደርጉ መሠረታዊ ምክንያቶች እንደሆኑ ይሰማናል።

    ለ. ከህግ ጋር ንክኪ ያላቸው ሕጻናት የቤት ውስጥ ጥቃት፣ በቤተሰብ የሚደርስ ጥቃት እና ከትምህርት መገለልን ጨምሮ ሌሎች በርካታ እና ተደራራቢ የጥቃት ዓይነቶች ይገጥሟቸዋል፤ ይህም በሕጻናቱ የአእምሮ ጤና ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊኖረው እንደሚችል ይሰማናል።

    ሐ. የፍትህ ሥርዓቶች ለሕጻናት መብቶች ቅድሚያ አይሰጡም፤ ይህም ብዙ ሕጻናት በፍትህ ስርዓት ውስጥ በማለፋቸው ምክንያት ጉዳት እንዲደርስባቸው፤ ችላ እንዲባሉ እና ስሜታቸው እንዲጎዳ ያደርጋል።

    መ. የወንጀል ፍትህ ሥርዓቶች መልሶ ከማቋቋምና ሰላም እንዲመለስ ከማድረግ ይልቅ ብዙ ጊዜ የሚያተኩሩት በቅጣት እና በመኮነን ላይ ነው።

12. ከፍትህ ስርዓቶች ጋር ንክኪ ላላቸው ሕጻናት እውነተኛ ለውጥ ለማምጣት መንግስታት እና የሲቪል ማህበረሰቡ ከህፃናት እና ወጣቶች ጋር በጋራ በመስራት ሁሉም ሕጻናት በአለም አቀፍ ህግ የተደነገጉ መብቶቻቸው መከበራቸውን እንዲያረጋግጡላቸው  እንጠይቃለ።

13. የሚከተሉትን ደግሞ በተለየ ሁኔታ  እንጠይቃለን፤

ሀ. ሁሉም ሕጻናት አካታች በሆነ እና ማንንም በምንም ምክንያት በማያገል መልኩ ፍትህን በእኩልነት እንዲያገኙ፤

ለ. ሕጻናት ሃሳባቸውን ለማካፈል እንዲችሉ ነጻነት እንዲሰጣቸው እና ሀሳባቸውም በቁም ነገር እንዲወሰድላቸው፤

ሐ. ሕጻናት በራሳቸው ህይወት ለመወሰን ያላቸው አቅም እንዲታወቅላቸው፤ ከአዋቂዎችም በቂ ድጋፍ እንዲያገኙ፤

መ. ሕጻናት ከወቅቱ ወረርሽኝ ጋር በሚመሳሰል መልኩ ተለዋዋጭ የሆኑ ሁኔታዎችን እና አደጋዎችን እንዴት በተሻለ ሁኔታ ማስተናገድ እንደሚችሉ መረጃ እና መመሪያ እንዲሰጣቸው፤

ሠ. ከህግ ጋር ንክኪ ያላቸው ሕጻናት ሰብአዊ በሆነ፤ መብቶቻቸውን ባከበረ እና ለአእምሮ ጤናቸውና ለደህንነታቸው ሲባል ሁሉን አቀፍ ድጋፍ በሚያገኙበት አግባብ እንዲስተናገዱ፤

ረ. የሕጻንነት እድሜያቸውን የጨረሱ ከህግ ጋር ንክኪ ያላቸው ወጣቶች ከሕጻናት ጋር ተመሳሳይ የሆነ ድጋፍ እንዲሰጣቸው፤

ሰ. ሕጻናትና ወጣቶች restorative justice ሂደቶች እንዲማሩ እና እንዲሳተፉ እድል እንዲመቻችላቸው።

ሸ. በፍትህ ስርዓቶች ላይ ያለው እምነት እንዲያቆጠቁጥ ለማድረግ ቁልፍ ሚና ስላለው ሕጻናት እና ወጣቶች መብቶቻቸውን እንዲጠይቁ ድጋፍ እንዲደረግላቸው ።

14. እውነተኛ የሕጻናት ፍትህን ማረጋገጥ የሚቻለው ሁሉም ሕጻናት በእኩልነት ሲስተናገዱ እና የሰብአዊ መብቶች ቃል ኪዳኖችን ተግባራዊ ለማድረግም ከአዋቂዎች ጋር በመተባበር ሊሰሩ የሚችሉበት ምቹ ሁኔታዎች ሲፈጠሩላቸው መሆኑን እናምናለን።

በመሆኑም እኛ የአለም ጉባኤ አዘጋጆች፣ አጋሮች እና ተሳታፊዎች በጋራ በመሆን መንግስታትንና የሲቪል ማህበረሰቡን ጨምሮ ሁሉም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ጥሪ እናደርጋለን።

## ዛሬም ሆነ ነገ የሕጻናት ፍትህ እንዲሟላ በቅንነት መስራት፤

15. መደበኛ የሆነው የሕጻናት ፍትህ ማዕቀፍን ለማበጀት እና የፍትህ ተደራሽነትን ለመዘርጋት፤ የህግና የቁጥጥር አሰራር ማዕቀፍ ለመገንባት፤ አሰራሮችም ሆኑ የአሰራር ሥርዓቶት ተግባራዊ እንዲሆኑ ለማድረግ፤ አግባብነት ያላቸውን ተቋናዮች አቅም ለመገንባት እና የባለግዴታዎችን፡ የማህበረሰብ አባላትንና የሰፊው ማህበረሰብን ተጠያቂነት ለማስፋን ጨምሮ ከሕጻናት ጋር የሚሰሩ አጋሮች እንደባለሞያ እና እንደማእከላዊ ተዋናይ ሥርዓትን ለመዘርጋትና አዎንታዊ ለውጦችን ለማምጣት በዓለም ዙሪያ ያሉ ሕጻናት ፍትህን በእኩልነት፤ ያለመድልኦ እና አካታች በሆነ መልኩ እንዲያገኙ ለማድረግ ሕጻናት እና አዋቂዎች ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘው እንዲሰሩ ማድረግ።

16. ለሕጻናት ምቹ የሆኑ፤ ሥርዓተ ፆታን ከግምት ያስገቡ፤ አካል ጉዳተኝነትን ያካተቱ መመሪያዎችንና ስለህጎችና አሰራሮቻቸው ያሉ መረጃንዎችን በማቅረብ፤ ሕፃናትና አዋቂዎችን ጨምሮ ስለሕጻናት መብቶች የማህበረሰቡን ግንዛቤ በማሻሻል፤ ሕጻናትን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመድረስ የሚያስችሉና እነርሱን ማዕከል አድርገው የተዘጋጁ መረጃዎችን በማመቻቸት፤ እንዲሁም ከህግ ጋር ንክኪ ያላቸውን ሕጻናት ጨምሮ ሁሉም ሕጻናት ሊሳተፉ የሚችሉበት አካታችና ተደራሽ የሆነ የተሳትፎ አሰራር እንዲኖር በማድረግ ሕጻናት እንደመብት ባለቤት የለውጥ ሀዋሪያ ሆነው እንዲሰሩ የሚያስችላቸውን ሁኔታ ማሻሻል እና የዛሬውን እና የወደፊቱን ድምጾችን ማጉላት፤

17. የሕጻናት ተሳትፎን ከማበረታታት ባለፈ እና በተለይም በመድልኦ፤ ለመገለል፤ ባላቸው ተጋላጭነት ወይም ባሉበት አደገኛ ሁኔታ ምክንያት ከምክክሮች የተገለሉ ከህግ ጋር ንክኪ ያላቸው ሕጻናትን አሳታፊ ባልሆነ እና ተሳትፊዋል ለማስባል ብቻ በሚደረጉ ውይይቶች ላይ ከማሳተፍ ባለፈ ሕጻናት በውይይት ጠረጴዛዎች ላይ ተገቢው ቦታ ተሰጥቷቸው እንዲሳተፉ ለማስቻል የሕጻናት ተሳትፎን በህግ መደንገግና ህጉንም ተፈፃሚነት እንዲኖረው ማድረግ፤

## ለሕጻናት መድሎ የሌለበት አካታች ፍትህን ተደራሽ ማድረግ

18. ከህግ ጋር ንክኪ ባለው እያንዳንዱ ሕጻን ላይ አሉታዊ ፍረጃን እና ማግለልን በሚያጠፋ መልኩ የሚፈፀም መድልኦን ማስወገድ እንዲቻል ባለመመጣጠን እና በመድልኦ ላይ በስፋት የተንሰራፋውን ፅንሰ ሀሳብ በማንኛውም ውይይቶችና የሕጻናት ፍትህ ማሻሻያዎች ላይ ማእከላዊ የውይይት አጀንዳ እንዲሆን ማድረግ፤

19. የወንጀል፣ የፍትሐ ብሔር፣ የአስተዳደር፣ የባህላ/የልማድ፣ የሽግግር እና የማህበራዊ ፍትህን አጠቃሎ ባቀፈ መልኩ ሁሉም ሕጻናት በተለይም በተገለሉ ቡድኖች ውስጥ ያሉ ሕጻናት እኩል እና ፍትሃዊ የፍትህ ተጠቃሚ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

20. ከህግ ጋር ንክኪ ላላቸው ሕጻናት ሁሉ እድሜን ያማከለ፣ አካል ጉዳተኝነትን ያካተተ፣ ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ የሚሰጥ፣ እና ልዩ ፍላጎቶችንና መብቶችን መሰረት ያደረጉ የፍትህ የአሰራር መስፈርቶችን እና መገልገያዎችን ለአካባቢያዊ ሁኔታው ተስማሚ እንዲሆኑ በማድረግ እና የአእምሮ (neuro) እድገትንና የባህሪ ሳይንስን መሠረት በማድረግ ማዘጋጀት እና መጠቀም።

21. ከህግ ጋር ንክኪ ያለውን የእያንዳንዱን ሕጻን የባህል እና የቋንቋ ብዝሀነትን የሚያከብር እና ችግሩን የሚፈታ እርምጃ ተግባራዊ ማድረግ፤

22. ማህበረሰቡ አዳዲስ መንገዶችን በመጠቀም በራሱ ተግባራዊ የሚያደርጋቸው እና ለሁሉም ሕጻናት መድልኦ በሌለበት እና አካታች በሆነ መልኩ ተደራሽ የሚሆኑ ማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎቶችን እና ነፃነት ከመንፈግ በመለስ ያሉ የእርምት እርምጃዎችን መመስረት፤

23. ከነባር ሕዝቦች ተወላጅ የሆኑ፣ አናሳ በሆኑ እና በተገለሉ የማህበረሰብ ክፍል ውስጥ ያሉ ህጻናት እንዴት ከህግ ጋር እንደሚነካኩ፣ የፍትህ ተጠቃሚነታቸው እንዴት እንደሚደናቀፍ እና በፍህት ሥርዓቱ በእነዚህ ሕጻናት ላይ አሉታዊ በሆነ መልኩ የሚፈፀሙ የልዩነት አሰራሮች ዋና መንስኤዎችን ለመረዳት የሚያስችሉ በሀገር አቀፍና በክልል ደረጃ መረጃ የማስብሰብና የዳሰሳ ጥናት የማድረግ ስራን ማስቀጠልና ማጠናከር፤ ይህም እነዚህ ሕጻናት በሥርዓቱ ውስጥ ከሌላዉ በተለየ በብዛት እንዳይገኙ ለመከላከል እና አግባብ በሆነ መረጃ የተደገፈ፤ ውጤታማ የሆነ እና ዘላቂነት ያለው ስራን ለመስራት ያግዛል።

24. መድልኦ የሌለበትና አካታች የሕጻናት የፍትህ ሥርዓት እንዲኖር እና ለሁሉም ሕጻናት ፍትህን በእኩልነት ማድረስ እንዲቻል፤ ይህንንም አግባብነት ያለው፤ በቂ የሆነና ፍትሀዊ የሆነ ሀብትና ጊዜ በመመደብ እንዲሁም ከህፃናት ጋር ግንኙነት ያላቸው ሁሉም አካላት ተገቢውን የአቅም ግንባታ ድጋፍ እንዲያገኙ በማድረግ ጉዳዩ ከፍተኛ የፖለቲካ ትኩረት ማግኘቱን ማረጋገጥ፤

## በቀውሶች እና በወረርሽኞች ወቅት ችግሮችን ተቋቁሞ የሚዘልቅ ተደራሽ የሕጻናት ፍትህ

25. በአደጋ ጊዜም ሆነ አደጋ በሌለበት ጊዜ ፍትህን ለሁሉም ሕጻናት በዘላቂነት ተደራሽ ማድረግ እንዲቻል አዳዲስ አሰራሮችን እና ችግርን መቋቋም የሚችሉ የፍትህ ሂደቶችንና ሥርዓቶችን የሚያበረታቱ የህግ እና የፖሊሲ ማዕቀፎችን ተግባራዊ ማድረግ፤

26. የአሰራር ሥርዓቶችን ደህንነት በሚጠብቅና በአካል በመገኘት የሚካሄደውን የፍትህ አሰጣጥ ሂደት በሚደግፍ አግባብ፤ በዲጂታልና በመልክአምድር ልዩነት፤ በተደራሽነትና አካታችነት፤ ደህንነትንና ሚንጥራዊነትን እንዲሁም የሕጻኑን ፈቃድና ምቾት ከግምት በማስገባት በተግባር ሙከራ የተደረገበትንና ውጤታማነቱ የተረጋገጠን ቴክኖሎጂ በመጠቀም ፍርድ ቤቶችን፤ የክርክር ሂደቶችን፤ ቃለ-መጠይቆችን፤ የጉዳይና የመረጃ አስተዳደሮችን እንዲሁም ሌሎች ሂደቶችን በበይነ-መረብ አማካኝነት ተግባራዊ ማድረግ፤

27. ተቋማት እና የተለያዩ የሴክተር መ/ቤቶች በአደጋ ጊዜ በትብብር የሚያዘገጁት እቅድና የሚሰጡት ምላሽ የሚመሩበትን ግልፅ የሆኑ መመሪያዎችን ( protocols) ማውጣትና መተግበር፤ በአደጋ ጊዜና በወረርሽኝ ወቅት በሕጻናት ጥበቃ እና ፍትህ ዙሪያ የሚሰሩ አካላትም ወሳኝ አገልግሎቶችን እንደሚሰጡ ተቆጥረው ፈቃድ እንዲሰጣቸውና ትኩረት ተሰጥቷቸው እንዲሰሩ ማድረግ፤

28. የፍትህ አካላት በአደጋ ጊዜ በፍጥነት ከሚለዋወጠው ሁኔታ ጋር ራሳቸውን አስተካክለው መስራት እንዲችሉ እና አሰራሮችንና አጋዥ ሰነዶችን በፍጥነትና ውጤታማ በሆነ መልኩ መተግበር እንዲችሉ አቅማቸውን ቀጣይነት ባለው አግባብ መገንባት፤

29. ቀውስ እና ወረርሽኝ ከሕጻናት መብቶች እና ፍትህን ከማግኘት እድሎች ጋር በተገናኘ የሚያስከትሏቸውን ተፅኖዎችና ችግሮች ማለፍ የሚቻልባቸውን ዘዴዎች የሚያመላክቱ መረጃዎችን ለሕጻናት ምቹ በሆነ፤ ሥርዓተ-ፆታን ባማከለ እና አካል ጉዳተኝነትን ባካተተ መልኩ ማዘጋጀት፤

## ከህግ ጋር ንክኪ ያላቸው ሕጻናት ምቹ የሆነ ፍትህ ስለማግኘት

30. ሕጻናት ከፍህት ሥርዓቱ ጋር የሚገናኙበትን አላስፈላጊ ሁኔታ በሚቀንስ አግባብ በሴክተር መ/ቤቶች እና በባለድርሻ አካላትመካከል በጥምረት የሚሰራ የቅንጅት አሰራርን በመመስረት ሁሉን አቀፍ የሕጻናት ፍትህ አስተዳደር አሰራርን መፈለግ፤

31. በማንኛውም ሁኔታ ከህግ ጋር ንክኪ ያላቸው ሕጻናትን የግል ፍላጎት፤ ማንነትን እና አስተዳደግን፤ ሕጻናቱ ያሉበትን ሁኔታና የእድገት ደረጃ ያማከለ ምቹ፤ ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ የሚሰጥ፤ አካል ጉዳተኝነትን ያካተተ፤ ስለስሜት ቀውስ መረጃ ያለው እና ለአካባቢው ተስማሚ የሆነ የፍትህና የማህበራዊ አገልግሎትን፤ መረጃን እና ሌሎች የህግና ሌሎች ድጋፎችን መስጠት፤

32. ከህግ ጋር ንክኪ ያላቸው ሕጻናትና ቤተሰቦቻቸው ባሉበት ሁኔታ ውስጥ ሆነው ችግሩን እንዲቋቋሙ፤ እንዲለምዱ እና ራሳቸውን እንዲቀይሩ ለመርዳት ተደራሽ የሆነ የእእምሮ ጤና እና የስነልቦና ድጋፍ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፤

33. ሕጻናትን ከህግ ጋር እንዲገናኙ የሚያደርጉ መንገዶችን ለመዝጋት፣ ወደጥፋት የሚመሩ ባህሪያትን ለመከላከልና ከባህሪያቱ ጋር ተያይዘው የሚመጡ አደጋዎችን ለመቀነስ፤ እንዲሁም ሕጻናት ከጥቃትና ከተጋላጭነት ነፃ የሆነ ሰላማዊ ኑሮ እንዲኖሩ ለማስቻል ዉጤታማ የሆነ ቅድመ ጥንቃቄ ስራዎችን፤ ሁሉን አቀፍና አካታች የቤተሰብ ድጋፍና ማጠናከር አገልግሎቶችን እና የማህበራዊ አገልግሎቶችን በማጠናከር ማህበረሰብን ለመገንባት የሚያስችሉ ስራዎችን በመለየት ተግባራዊ ማድረግ፤

34. ከህግ ጋር ንክኪ ያላቸው ሕፃናት ሁሉን አቀፍ በሆነ፣ በተቀናጀ እና የእያንዳንዱን ሕጻን ጉዳይ ማስተዳደር በሚቻልበት አግባብ (ማለትም ሁሉንም ለይቶ በአንድነት ከማየት በተለየ መልኩ) restorative justice ከመደበኛው የፍትሕ ስርዓት ውጭ የማረም ሂደትን፤ መልሶ ማቋቋምን እና መልሶ የማቀላቀል ሥራን ቅድሚያ መስጠት፤

35. በሕጻናት ጥበቃ፤ በማህበራዊ ጥበቃ፤ በጤና ድጋፍ፤ በአእምሮ፤ በስነልቦና በማህበራዊ ጤና እንዲሁም ለአደንዛዥ እፅ ወንጀል በአማራጭነት መፍትሄ ሆኖ የተቀመጠውን ሁሉን አቀፍ አገልግሎት ጨምሮ ሌሎች አማራጮችን በመጠቀም የተሻለ መፍትሄ ሊያገኙ የሚገባቸውን እና መፍትሄ ሊያገኙ የሚችሉትን የሕጻናት ባህርያትን የወንጀል ድርጊት ሆነው እንዳይቆጠሩ ማድረግ፤ እና

36. ለ21ኛው ክፍለ ዘመን የሚመጥኑ ብቁ የሕጻናት ፍትህ፤ የሕጻናት ጥበቃ እና ሌሎች ሰራተኞችን በተለይ ደግሞ የህግ ባለሞያችን፤ የህግ አስፈፃሚ አካላትን፤ አቃቤ ህጎችን፤ ማረሚያ ቤት ሰራተኞችን እና የማህበራዊ አገልግሎት ስራተኞችን አቅም በሕጻናት እድገት፤ ሕፃናትን ምቹ በሆነ መንገድ የመጠየቅ ዘዴዎች፤ ለድጋሚ የስሜት መታወክ የሚያጋልጡ አሰራሮችን ለመከላከል ስለተቀመጡ ድንጋጌዎች እና በግልጥ ሳይታወቅ ተግባራዊ ሊሆን የሚችልን ወገንተኝነት ለመከላከል ስለሚያስችሉ ዘዴዎች ልዩ ስልጠናዎችን ማዘጋጀት፤ የትምህርት ካሪኩለሞችን ማሻሻል እና አገልግሎቶችን ለማሻሻል የሚያስችሉ አዳዲስ ፈጠራዎችን ማበረታታት።

## ድጋፍ ሰጪዎች

ግሎባል ኢኒሼቲቭ ኦን ጀስቲስ ዊዝ ችልድረን (Global Initiative on Justice With Children) የተለያዩ ዓለምአቀፍ ተቋማት በጋራ በመሆን ያዘጋጁት ፕሮግራም ሲሆን ዓለምአቀፍን የሕጻናት ፍትህ ጉባኤን በማዘጋጀት ፊር ቀዳጅ ሚና ይጫወታል፤ ፍትህ ለሕጻናት በሚል በበይነ-መረብ አማካኝነትም በዓለም ያሉ ባለሞያዎችን ያሳትፋል፤ ያስተባብራል። በሕጻናት ፍትህ ዙሪያ በይነ-መረብን በመጠቀም እንዲሁም ለአስተያየት፤ ለሀሳብ መለዋወጥ እና ቀጣይነት ያለውን የመማማር ሂደትን በማጠናከር ውይይቶችንና ትግበራዎችን የማበረታታትና የማመቻቸት አላማ አለው።

የዓለም አቀፉ የሕጻናት ፍትህ ጉባኤ የተቀረፀውም ከህግ ጋር ንክኪ ወይም ግንኙነት ላላቸው ሕጻናት ያሉባቸውን ወቅታዊ ችግሮች ለመፍታት ሲሆን፤ መድረኩም ለሕጻናትና ለወጣቶች፤ ለፖሊሲ አውጪዎች እና በፍትህ ዘርፍ ውስጥ ባሉ ባለድርሻ አካላት፤ ለትምህርት ተቋማት፤ ለሲቪል ማህበረሰብ እና ለተባበሪት መንግስታት ድርጅት ተወካዮች እንዲሁም ለሌሎች ባለሞያዎችና ሰራተኞች የተለየና የሚሰራ ቦታን ያመቻቻል። (1) ፍትሃዊ እና ተገቢ የፍትህ ስርዓቶችን በዓለም ዙሪያ ላሉ ሕጻናት እና ከሕጻናት ጋር ማሳደግ; (2) ለባለሙያዎች ምርጥ ተሞክሮዎችን ለመለዋወጥ፣ ሳይንሳዊ ትብብርን ለማጎልበት፣ የፖሊሲ ምክሮችን ለመቅረጽ እና ለሕጻናት የፍትህ ግንዛቤን ለማሳደግ የሚያስችል ቦታ መስጠት፤ እና (3) ከህግ ጋር ንክኪ ያላቸውን ሕጻናት እና ወጣቶች መብቶች የአለም አቀፍ ሰነዶችን በተግባር ላይ ለማዋል መደገፍ.

እ.ኤ.አ. የ2021 የአለም የሕጻናት ፍትህ ጉባኤ ትኩረት ያደረገው የፍትህ ስርአቶችን ተደራሽነትን በሚቀንሱ እና የፍትህ ሥርዓት ጥራትን የሚጎዱአድሎዎችን ለመቀነስ እና ሁሉም ሕጻናት በህግ ፊት እኩል የመስተናገድ ዋስትና እንዲኖራቸው ለማረጋገጥ የሚያስችሉ በተግባር ላይ ያተኮሩ ስትራቴጂዎችን በመለዋወጥ ላይ ነበር። ተሳታፊዎች በዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ደረጃ በተካሄዱ የጋራ ውይይቶች፣ በተሞክሮዎች ላይ ያተኮሩ የፓናል ውይይቶች፤ በተመሰከረላቸው ስልጠናዎች እና በፖሊሲ ላይ ባተኮሩ የቡድን ውይይቶች ላይ ተሳትፈዋል። በአለም አቀፉ ጉባኤ " የፍትህ ተደራሽነትን ለሁሉም ሕጻናት ማረጋገጥ-መድልኦ ወደሌለበትና አካታች ወደሆነ የሕጻናት የፍትህ ሥርዓት" በሚለው አጠቃላይ መሪ ቃል ውስጥ 11 ንዑስ ርዕሰ ጉዳዮች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ነበር።

- ሥርዓታዊ ዘረኝነት እና ከነባር ሕዝቦች፣ ከጎሣ እና ከሌሎች አናሳ ቡድኖች ውስጥ የወጡ ሕፃናትን ያለአግባብ መወንጀል
- በፆታ፣ በፆታዊ ዝንባሌ እና በፆታ ማንነት ምክንያት የሚደረግ መድልዎ፡ የስርዓት-ፆታ ፍትህ አቀራረብን ማጎልበት;
- በስደት ምክንያት ህጻናት እና ወጣቶች ላይ የሚደርስ መድልዎ፣ ስደተኞችን፣ ከቤተሰብ ተለይተው ለሚሰደዱ የውጭ ሀገር ልጆች እና የውጭ አገር ወላጅ ያላቸው ልጆችን ጨምሮ;
- በአካል ጉዳት እና በጤና ሁኔታዎች ምክንያት የሚደረግ መድልዎ;
- በአደንዛዥ እፅ አጠቃቀም እና አላግባብ መጠቀም ምክንያት የሚደረግ መድልዎ;
- የሕፃናትን የበይነመረብ ባህሪዎችን መወንጀል
- የዕድሜ ገደቦች እና የሁኔታ ጥፋቶች;
- በሕፃናት ፍትህ ስርዓቶች ውስጥ የሕፃኑ ድምጽ እንዲሰማ ማድረግ;
- በህጋዊ ብዝሃነት ሁኔታዎች ውስጥ የሕፃናትን መብቶች ማሟላት;
- በአደጋ እና ወረርሽኞች ጊዜ ችግሩን ተቋቁሞ የሚዘልቅ የሕፃናት ፍትህ ስርዓቶችን መገንባት; እና
- በሕፃናት ፍትህ ስርአቶች ውስጥ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን መፍታት እና ለሕፃናት የወንጀል ሰለባዎች፣ በወንጀል ውስጥ ለሚገቡ እና ምስክሮች ለህጻናት ተስማሚ የሆኑ አቀራረቦችን ማረጋገጥ።

ይህ የሕጻናት ፍትህ ዓለም አቀፍ መግለጫ የተረቀቀው በአለም አቀፉ ጉባኤ ቅንጅት እና በሕጻናትና ወጣቶች አማካሪ ቡድን ሲሆን፤ ከሳይንሳይንቲፊክ ኮሚቴ ግብአቶች፣ አጋሮች እና የአለም ጉባኤ እና ቀድሞ ከተደረጉት የዝግጅት ስብሰባዎች ላይ ከተሳተፉ ተሳታፊዎች የተገኘውን ግብዓትም አካቷል።

ለበለጠ መረጃ፡ www.justicewithchildren.orgን ይጎብኙ።

ይህ ሰነድ ዋናው የእንግሊዝኛ ቅጂ የማህበረሰብ ትርጉም ነው። ስህተቶችን ካገኙ በ info@justicewithchildren.org እንድታሳውቁን በአክብሮት እንጠይቃለን።